የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ የካቲት ፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.32
ADDIS ABABA 15th February, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፱/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

ለልማት ፖሊሲ ፋይናንስ ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……….ገጽ ፲፩ሺ፬

## Content

Proclamation No.1099/2019

International Development Association Financing Agreement for Financing Development Policy Proclamation.....Page 11,004

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፱/፪ሺ፲፩

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማትማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለልማት ፖሊሲ ፋይናንስ ማስፈፀሚያ የሚውል ፬፻፴ ሚሊዮን ፩፻ ሺህ ኤስ.ዲ.አር (አራት መቶ ሰላሳ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የገንዘብ መጠን የሚያስገኝ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ጥቅምት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕዳር ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1099/2019

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS,** a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 430,100,000 Special Drawing Rights (Four Hundred Thirty Million One Hundred Thousand SDR) Credit; for financing Development Policy was signed in Addis Ababa on the 2nd day of November, 2018;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on the 4th day of December, 2018;

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:



www.chilot.me

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለልማት ፖሊሲ ፋይናንስ ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፱/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ጥቅምት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 6336-ET ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፬፻፴ ሚሊዮን ፩፻ ሺህ ኤስ.ዲ.አር (አራት መቶ ሰላሳ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) ብድር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲያውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፰ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Financing Development Policy Proclamation No. 1099/2019".

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Number 6336-ET signed in Addis Ababa on the 2nd day of November, 2018 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 430,100,000 Special Drawing Rights (Four Hundred Thirty Million One Hundred Thousand SDR) Credit; in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of February, 2019.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me